# የኢትዮጵያ የታሪክ ፈተናዎች፡ አልታረቅ ያሉ ሕልሞችና የኢህአዴግ ቆርጦ-ቀጥል ፖለቲካ

## በዋሽግንቴን ዲሲ ለቪዠን ኢትዮጵያ ይቀርብ የነበረ ጹሑፍ

## (በመረራ ጉዲና (ዶ/ር)

- *መንደርደሪያ ሀሳቦች*

*የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ባለሳምንት የሆነው ኢሕአዴግ፣ የደርግ ተመሳሳይ ዕድል ይግጠመው፤ አይግጠመው ባይታወቅም፤ አሁን ባለው ሁኔታ በሚሠራቸው ሥራዎች ውስጥ ከደርግ ያላነሱ ባዶ የመፈክር ጫጫታዎች ይበዙበታል፡፡ ሕልሞቹም የኢትዮጵያውያን የጋራ ሕልም መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ብዙ ነገሮች የሉበትም፡፡ በአሥር ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እንገባለን ተብሎ ከበሮ ቢመተም በዓለም ደረጃ በሚወጡ መረጃዎች ኢትዮጵያቸን አሁንም የዓለም ጭራ ከሆኑት ሀገሮች ተርታ ናት፡፡*

*ይህ ጹሁፍ እንደሚያሰየው፤ የሀገራችን ፖለቲካ ከገባበት ቅርቃር ውስጥ የሚወጣው ወይ እኛ ኢሕአዴግን ከገባበት ቅርቃር ለማስወጣት የሚያስችል የተባበረ ትግል ውስጥ በቁርጠኝነት መግባት አለብን፣ ወይ የኢሕአዴግ መሪዎች ከንጉሡም፣ ከደርግም ተምረው ከሌሎች ኃይሎች ጋር ብሔራዊ መግባባት ፈጥረው ሀገሪቷንና ሕዝቦቿን ለመታደግ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ እዚህ ላይ ተቃዋሚዎችም ሁሌ የፖለቲካ ቅርቃር ውስጥ እየዳከርን፣ ሥልጣንን እንደልቡ የሚጠቀምበት፤ የሕዝብን ሀብትና ንብረትን እንደፈለገው የሚጫወትበትና ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠረው ሠራዊት ያለው ኢሕአዴግ ቀድሞ ይለወጣል ብሎ መጠበቅ የፖለቲካ የዋህነት መሆኑን መረደትም መሰራታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ኢሕአዴግን ጭምር ለመታደግ፣ በዚህ ጽሑፍ እንዳማነሳው የምር የቤት ሥራዎቻችንን መሥራት ይኖርብናል፡፡ ሁሌ የራሳችንን የቤት ሥራ ሳንሠራ፤ የኢሕአደግንም ሆነ የፈረንጆቹን በሮች ማንኳኳቱ የትም እየወሰደን እንደልሆነ አጣያያቅ ጉደይ አይመሰልኝም፡፡ ፖለቲካ ለሚገባው ሰው እስካሁን ያለው የዓመታት ተሞክሮዎቻችንም ይኸው ነው፡፡*

*ሌላው በውል መገንዘብ ያላብን ጉዳይ፤ እሰካሁን ተቃዋሚዎችም በተደጋጋሚ ከገበቡት የፖለቲካ ቅርቃር ውስጥ ለመውጣት የተደረጉ ጥረቶችም እንዳልተሳኩ ይታወቃል፡፡ አንጋፋ  በሚባሉ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች መኢሶንና ኢህአፓ የተከፈተው የመከፋፈል ፖለቲካ ዛሬም በስፋት ቀጥለዋል፡፡ አንዱ ቀዳዳ ሲዘጋ ሌላው ቀዳዳ እየተከፈተ መፍትሄው ለወዳጅም፣ ለጠላትም እያስቸገረ ነው፡፡ እንደውም ተቃዋሚዎች ዛሬ ለኢሕአዴግ የከፋፍለህ ግዛ ሜራ የበለጠ ተጋልጠዋል፡፡ የቆዩት የክፍፍል መስመሮች መፍትሔ ሳያገኙ፤ አዳዲስ የክፍፍል መስመሮች እየተጨመሩ መጥተዋል፡፡ ኢሕአዴግ የፈለፈላቸው ወይም ገዝቶ ከተቃዋሚነት ጐራ ያስወጣቸው ዋናው ሥራቸው የተቃዋሚዎችን ክፍፍል ማስፋት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ፣ የሀገራችን ፖለቲካ ከኢሕአዴግ ጭምር በሦስትዮሽ መሥመር ክፍፍል የተወጠረ ነው፡፡ የብሔር ጥያቄን የሚቀበሉና የማይቀበሉ ቅራኔ አላቸው፡፡  የኢትዮጵያን አንድነት የሚቀበሉና*

የማይቀበሉ የብሔር ንቅናቄዎች አሉ፡፡ የሰላማዊ ትግል ተከታዮችና የትጥቅ ትግል አቀንቃኞች አሉ፡፡ በየድርጅቶቹ እግር ጥሎዋቸው ከግል ዝና ያለፈ የፖለቲካ ዓላማ የሌላቸው ግለሰቦችም አሉ፡፡ ተባብሮ መታገል እልህ አስጨራሽ ሥራ የሆነው በነዚሁ ምክንያቶች መሆኑ ብዙም አያከራክርም፡፡ በተለይ የሚጋጩ ሕልሞችን ይዞ የተባበረ ትግል ውስጥ መግባት ቀላል ጨዋታ አልሆነም፡፡

ይባስ ብሎ የተቃዋሚዎች ክፍፍል በኢሕአዴግ ደህንነቶች እይታ ሥር ከሚንቃሳቀሰው ይልቅ ከኢሕአዴግ ቁጥጥር ውጭ የሚንቃሳቀሰው የዲያስፖራው ዓለም ውስጥ በጣም ሰፍቶ መገኘቱ ነው፡፡ ሀገር ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ጭምር የሚቆረጡትና የሚሰፉት በዲያስፖራው ተጽእኖ ጭምር መሆኑም አጣያያቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ የዲያስፖራ ወንድሞቻችን በሕልም ዓለም ከመኳተን አልፈው ለምን ድርጅቶችን እንደሚያፈርሱ፣ የሚያውቁ አይመስለኝም፡፡ አጉል ሕልም፣ አጉል ሥራ ስለሚያሠራ፣ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች በሚያሳዝን መንገድ ሜዳ ላይ ተበትነው ቀርተዋል፡፡ በተለይ የብሔር ፖለቲካው እስኪበጠስ የተወጠረው በዲያስፖራው ዓለም ነው፡፡ የኢንተርኔት ጦርነትም እስከጫፍ ድረስ የሚወነጨፈው በዚሁ የዲያስፖራ ዓለም ነው፡፡ በአንድ በኩል የተቃዋሚው ኃይል ከገባበት የመንታ መንገድ የፖለቲካ ቅርቃር እንዲወጣ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እምቅ የሆነውን የዲያስፖራን ሀብት በአግባቡ ለሕዝባችን የነፃነት ትግል እንዲውል በውጭው ዓለም ያሉ የተደራጁም ሆኑ ያልተደራጁ ልሂቃን የአጋዥነት ሚናቸውን በትክክል አውቀው ሀገር ውስጥ ካሉ ሐቀኛ ኃይሎች ጋር ትግላቸውን ማቀናበር መቻል አለባቸው፡፡ አለበዚያ ባልተናበበና ባልተቀናጀ መንገድ ትግሉ ይቀጥል ከተባለ፣ ደጋግሞ እንዳጋጠመን፤ የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች ከመሆን አያልፍም፡፡ ሁሉም የሀገሪቱ ሀቀኛ ለውጥ ፈላጊ ኃይሎች ትግሉን በዚህ መነጽር ማየታቸው ወሳኝ የሆነበት ጊዜ ላይ መድረሳችንን በውል ማጠን ጊዜው አሁን ይመስለኛል፡፡

በኔ እይታ፤ የተቃዋሚው ኃይል ከገባበት የፖለቲካ ቅርቃር (dead-end) ለመውጣት ራሱን እንደገና ማደራጀት ይኖርበታል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ አዲስ የመሰባሰብ እስትራቴጂ መቀየስ አለበት፡፡ ነጻ የሆኑ የተቃዋሚ ድርጅቶች (ኢሕአዴግ በቀጥታም ሆነ በሥውር እጆቹ የማይቆጣጠራቸው) በቁርጠኝነት የሀገሪቱን ችግሮች የሚፈቱበትን ዲሞክራሲያዊ ጨዋታ (democratic game) ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡ የእንዲህ ዓይነቱ ጨዋታ ውጤት የሚያመጣው በአንድ ቡድን ወይም ሁለት ቡድኖች የተረጋጋች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መፍጠር ይቻላል የሚለው ሕልም ሲቀር መሆኑን በውል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ቡደን ሥር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት ይቅርና፣ ትርጉም ያለው እድገትም ሆነ ሳላምና መረጋጋት እንኳ ማምጣት እንዳልተቻለ የቅርብ ታሪካችን በቂ ምስክር ነው፡፡ ኢሕአዴግ ከ24 ዓመታት በላይ የአንድ ቡድንን ሕልም አሳካለሁ ብሎ ራሱም ታምሶ ሕዝብን ቢያምስም፣ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ስትፈጠር እያየን አይደለም፡፡ ኢህአዴጎች ከሠሩት ሥራ የፕሮፖጋንዳ ጫጫታቸው እንደሚበልጥ የኢሕአዴግ መሪዎችም ያውቁታል፡፡ ወደ መቶ ሚሊዮን እየሆነ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕልምና ፍላጐቱ ከኢሕአዴግ መሪዎችና ካድሬዎቹ ሕልምና ፍላጐት በእጅጉ ይሰፋል፡፡ የኢሕአዴግ ዲሞክራሲ ደግሞ በኢሕአዴግ ቁመት የተሰፋ ጥብቆ ከመሆን አላለፈም፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታ የተቃዋሚው ኃይል እንደገና ራሱን ቢያደራጅ፣ የኢትዮጵያ የነፃነት ቀን ሩቅ አይመስለኝም፡፡ በሕዝቡ ተጅቦ እየተከሄደ ያለው የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ ይህንኑን የሚያመለክት ሀቅ ነው፡፡ የማይታረቁ ሕልሞቻችንን ተሸክመን በምኞች ፈረስ መጋለቡን ከቀጠልን ግን፤ ሕልሞቻችን ሕልም ከመሆን አያልፉም፡፡ የቡዳ ፖለቲካችንን ተሸክመን ላለፉት አርባ ዓመታት ኳትነናል፣ ለሚቀጥሉት አርባ ዓመታትም በያዝነው መንገድ ብንኳትንም የትም አንደርስም፡፡ ስለሆነም፣ በሐቅ የተቃዋሚ ኃይል ነን የምንለው፤ እስካሁን ላለፉት አርባ ዓመታት የሠራናቸውን ስህተቶች ባረመ መልኩ በአዲስ መንፈስ፣ በጋራ ሕልም ዙሪያ እንደገና በሀገር ውስጥም፤ ውጭም መደረጀት የግድ ይመስለኛል፡፡ ውጤት አልባ ለሆነው የተበታተነ ትግል የሚባክነውን የሀገር ሀብት ወንዝ ሊያሻግር ለሚችል የጋራ ትግል ማዋልም የግድ ነው፡፡ የሁላችንም የፖለቲካ መንግሥተ ሰማያት ሁላችንንም በእኩልነት የምታስተናግድ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር ለነገ የምንለው ጉዳይ መሆን የለበትም፡፡ በመጨረሻም የጋራ የታሪክ ፈተናችንን ለማለፍና የጋራ ሕልሞቻችንን እውን ለማድረግ የሰከነ ትግል፣ አቅም ላይ የተመሠረተ ትግል፣ የተደረጀና የተባበረ ትግል ውስጥ በሐቅ፤ በፍጥነትና በቁርጠኝነት መግባት እንደሚያስፈልግ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

- ***ተቃዋሚዎች በመንታ መንገድ ላይ፣ መፍትሔ ያጣው የቡዳ ፖሊቲካችን***

የቡዳ ጉዳይ በሀገራችን ባሕል ውስጥ የታወቀ ስለሆነ ለማስረዳት ዝርዝር ውስጥ አልገባም፡፡ ቡዳና ፖለቲካችንን ምን አገናኛቸው ለሚለው ጥያቄ ግን ተገቢ መልስ መስጠት ስለአለብኝ አንዳንድ ጭብጦችን ላስቀምጥ፡፡ ተረቱ እንደሚለው፣ አንድ ቡዶችን ለይቶ የማያውቅ ሰው፣ የቡዶች መንደር ይደርስና፣ ‹‹እዚህ አካባቢ የቡዶች መንደር አለ ይባላል፣ የትኛው ነው›› ብሎ ራሱን፤ ቡዳውን ይጠይቀዋል፡፡ ቡዳው ሰው፣ ‹‹ቡዶች የምንባለው እኛው ነን›› ለማለት ድፍረት ስላጣ፣ ‹‹እኛ እዛ ማዶ ያሉት ናቸው እንላለን፣ እነሱ ደግሞ እኛን ይሉናል›› አለ ይባለል፡፡ ላለፉት አርባ ዓመታት ለውጥ ለመምጣት ከአንድ ትውልድ በላይ ቀላል ያልሆነ መስዋእትነት ተከፍሎዋል፡፡ ነገር ግን የሀገራችን ፖለቲካ ባለህበት ርገጥ ከመሆን፣ አንዳንዴ ድግሞ የኋሊት ከመሄድ አላለፈም፡፡ ይበልጥ የሚያሰዝነው፤ ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ለፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ከከፈሉት በላይ ሀገራችን ለውጥ ለመምጣት ውድ ዋጋ ከፍላለች፣ የታሰበው ለውጥ ግን አልመጣም፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ጥያቄ ለሀገራችን ፖለቲካ ምስቅልቅል ጉዞ ኃላፊነቱን የሚወስደው ማነው? የሚለው ነው፡፡ ቢያንስ አንዱ በሌላው ላይ ጣት ከመቀሰር አልፎ የየድርሻችን እንኳ እንውሰድ ሲል አይታይም፡፡ እንደቡዳው፤ ስህተት የሠራሁት እኔ ነኝ ከማለት ይልቅ፤ አጥፊዎች እነዛ ናቸው ማለት ይቀላል፡፡ የአንድ ትውልድ ምርጦችን ያለርህራሄ የጨፈጨፈው መንግሥቱ ኃይለማርያም እንኳ ‹‹ሰው ይቅርና ዝንብ አልገደልኩም›› ነበር ያለው፡፡ ተባባሪዎቹ የነበሩ የደርግ ባለሥልጣናትም ያንን አስከፊ ግፍ የፈጸምነው ‹‹የሀገር ፍቅር ያንገበገበን ወታደሮች ነበርን›› እያሉ መጽሐፍ እየጻፉ ነው፡፡ የጥፋት ኃላፊነቱንም በሌሎች ላይ እየደፈደፉ ነው፡፡ ቢያንስ ብዙዎቹ በድንቁርና ለጨፈጨፋዋቸው ዜጎች ኃላፊነቱን ለመውሰድ አልተዘጋጁም፡፡

የቡዳ ፖለቲካችንን ከሁሉም በላይ አስቸጋሪ የሚያደርገው ሁሌም ጥፋተኞች እኛ ሳንሆን እነዛ ናቸው ብለን ስለምንደርቅ ነው፡፡ እዚህ ላይ ፈረንጆች የሚበልጡን በሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች ይመስለኛል፡፡ አንደኛው፣ ዛሬ በደረሱበት ደረጃ ጥፋት መቀበልን እንደሞት አያዩትም፡፡ ሁለተኛው፤ ሥልጣንን የሙጥኝ በማለት አጥፍቶ መጥፋትን ከባህላቸው አስወግደዋል ወይም የኋላቀሮች አስተሳሰብ አድርገውታል፡፡ ቢያንስ ከሂትለር ወዲህ የአብዛኞቹ ጉዞ በዚህ አቅጣጫ ነው፡፡ ሦስተኛው፣ ፖለቲካቸው በሰጥቶ መቀበል ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ሁሉንም አግኝ ወይንም ሁሉንም እጣ (zero-sum-game) የሚባለውን ፖለቲካ ከልብ እየተው መጥተዋል፡፡ ይበልጥ ደግሞ ከሥልጣን በኋላ፣ ጥሩ ኑሮ መኖርም፣ ክብር ማግኘትም እንደሚቻል አውቀዋል፡፡ እንደውም ከሥልጣን በኋላ ያለጭንቀት የተደላደለ ኑሮ መኖር እንደሚቻል ያውቃሉ፡፡ ኦባማ በአፍሪካ ኅብረት ንግግሩ የአፍሪካ መሪዎችን ለማስተማር የሞከረው ይህንኑ ነው፡፡ ትምህርቱ ገብቶት ይሁን፤ በተለመደው የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት የማስመሰል ፖለቲካ፤ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትርም ኦባማ ይህንን ሲናገር ሲያጨበጭብ አይቻለሁ፡፡

ሁላችንም መመለስ ያላብን መሰረታዊ ጥያቄ፤ ሥልጣን ላይ ያሉት ለሥልጣናቸው ሲሉ የቡዳ ፖለቲካችንን ጨወታ ቢቀጥሉ፣ ለለውጥ እንታገላለን የሚሉ ተቃዋሚዎች ከ1960ዎቹ ጀምሮ ለምን ከአንድ ትውልድ በላይ ከኛ ጋር ከኖረው የመከፋፈል ፖለቲካ አዙሪት መውጣት እንዳልቻልን ነው፡፡ ለአብነት፤ የቡዳ ፖለቲካችን (አንዱ ሌላውን የሚከስበት) የተጀመረው በአንጋፋዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶቻችን በመኢሶንና ኢሕአፓ መካከል ነበር፡፡ እነሱ የተፈጠሩበት የዛሬ 45 ዓመት ገደማ ይቅርና ዛሬ እንኳ የሁለቱ ድርጅቶች አባላት የስህተት ድርሻዎቻቸውን ውሰዱ ቢባሉ፣ በተገቢው የታሪክ ሚዛን ላይ አስቀምጠው ድርሻዎቻቸውን የሚወስዱ አይመስለኝም፡፡ ጥቂቶቹ እንዳሉ ቢታወቅም፤ አብዛኞዎቹ ከትግሉ የወጡና አሁን ካሉት የየድርጅቶቹ አመራር ጋር ድርጅታዊ ቁርኝታቸውን ያቆሙ ናቸው፡፡

ይህ የቡዳ ፖለቲካችን የዛሬ አርባ ዓመት አሰቃቂ እልቅት ውስጥ እንዳስገባን፣ ዛሬም ቀውስ ውስጥ እንድንዳክር እንዳደረገን አከራካሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ የበለጠ የሚያሰዝነው ደግሞ፤ በተለያዩ ጊዜያት ከዚህ የቡዳ ፖለቲካችን ለመውጣት ሰፊ ጥረቶች ቢደረጉም፤ ጥረቶቹ ከአርባ ዓመታት በኃላ እንኳ አልሳካ ማለታቸው ነው፡፡ እዚህ ላይ አንባቢው ልብ ሊለው የሚገባው ጉዳይ ላለፉት 40 ዓመታትና ከዚያም በላይ ያልተሞከረ የኅብረት ትግል እንደለሌ ነው፡፡ አንዳቸውም ሀገሪቷንና ሕዝቦቿን ለመታደግ አልቻሉም፡፡ አንዳንድ ድርጅቶች ለግላቸው ጥቅም ያገኙበት የኅብረት ሥራ ቢኖርም፣ ለሀገርና ለሕዝብ የጠቀሙበት ጊዜ የለም፡፡ ይህንን ነጥብ ትንሽ በዝርዝር እንመልከት፡፡

በሀገራችን ታሪክ በፖለቲካ ፓርቲነት የመደራጀት ሙከራ የተጀመረው በመኢሶንና ኢሕአፓ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ባለመታደል ሆኖ የመከፋፈል ፓለቲካውም የተጀመረው በእነሱ እንደሆነ ብዙም አያከራክርም፡፡ ሁለቱም ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በቀጥታ የወጡና የተማሪው ንቅናቄ የጋራ ትግል ቀጥተኛ ወራሽ ስለነበሩ ከልምድ ማነስ ውጭ የተባበረ ትግል ለመምራት የተሻለ ታሪካዊ ዕድል ነበራቸው፡፡ ሆኖም አልተጠቀሙበትም፡፡ የቡዳ ፖለቲካውን ሳንረሳ፣ ክፍሉ ታደሰ

(የኢሕአፓ አመራር አባል)፣ አንዳርጋቸው አሰግድ (የመኢሶን አመራር አባል) በዝርዝር እንደጻፉት የመኢሶኑ መሪ፣ ኃይሌ ፊዳ አልጄሪያ ድረስ እየሄደ በዋናነት ኢሕአፓን ከፈጠረው የብርሃነ-መስቀል ረዳ ቡድን ጋር ሲናጋገር ነበር፡፡ መግባባት ግን አልተሳካለቸውም፡፡ የዚህ የመጀመሪያው ተባብሮ የመታገል ጥረት መክሸፍ ኃይሌ ፊዳና ብርሃነ-መስቀል ረዳን ጨምሮ የአንድ ትውልድ ምርጦች ውድ የሕይወት ዋጋ ከፍለውበታል፡፡ ከደርግ እልቂት የተረፉት የሁለቱ ድርጅቶች መሪዎች ደርግ ከመውደቁ በፊት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዲኃቅ) የሚል ኅብረት ከሌሎች ጋር መፍጠር ችሎ ነበር፡፡ እንደአነሳሳቸው የመከፋፈል ፖለቲካን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመዝገት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ይፈጥራሉ ተብሎ ተስፋ ቢደረግም፣ የተሰሩበትን የታሪክ አጥር ሰብሮ መውጣት አልቻሉም፡፡ በአንድ ሰሞን ሞቅታ ሰማይ የነካው የነኮ/ል ጐሹ ቡድንም ዕድል እንዳልሰጣቸውም ይታወቃል፡፡ የጋራ ድርጅታቸው ኢዲኃቅ ተገቢ ቀብር ሳያገኝ አንድ እርምጃ እንኳ ወደፊት ሳይወስዳቸው ጡረታ ወቶዋል፡፡

መኢሶንና ኢሕአፓ ከዛም በኋላ በተለያዩ ጊዜ አንድ ላይ ለመሥራት ሞክረዋል፡፡ ነገር ግን አንድ ጊዜ ታሪክ የሰጣቸውን ዕድል ስላልተጠቀሙ፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክ ውስጥ የአንጋፋነት ሚና መጫወት አልተሳካላቸውም፡፡ የትግል ልምዳቸውንና እውቀታቸውን ለዛሬው ትውልድ ማውረስ አልቻሉም፡፡ በአዲሱ ትውልድም እየተገፉ እንደመጡ አጠያያቂ አይደለም፡፡ አሁንም ማንሠራራት ከቻሉ የትግል ልምዳቸው ቀላል አይደለም፡፡ በየትኛውም ሚዛን ከሚዳ እየተለቀሙ ለፖለቲካ ንግድ ሲባል ከሚፈጠሩ ድርጅቶች እጅግ በጣም የላቀ ሚና ሊኖራቸው እንደሚችል አከራካሪ ጉዳይ አይመስለኝም፡፡ የሠሩዋቸው  የፖለቲካ ስህተቶች እንዳሉ ሆኖ፣ አባሎቻቸው ለሆዳቸው ሲሉ እንዳልሞቱ ይታወቃል፡፡ መንገድ ቢጠፋባቸውም፣ እንደዛሬው የፖለቲካ ንግድ ሥራ ላይ እንዳልተሠማሩም አከራከሪ ጉደይ አይደለም፡፡

ኢሕአዴግ ከገባ በኋላ፣ የቡዳ ፖለቲካችን ብሶበታል ለማለት ይቻላል፡፡ በኢሕአዴግ ጭምር በመታገዝ የፖለቲካ ነጋዴዎች እየበዙ መጥተዋል፡፡ በአጭሩ ፖለቲካ በቀላሉ ትርፍ የሚታፈስበት የሸቀጥ ዕቃ እየሆነ መምጣቱን በአደባባይ ሕዝቡ እያየ ነው፡፡ የኢሕአዴግ አባላት ናቸው የሚባሉትን ከጨመርን፤ ፖለቲካው የሚሊዮኖች መተዳደሪያም እየሆነ፤ የፖለቲካው ዓለም ሰው ሳይሠራ የሚከብርበት ሆኗል፡፡ በዚህ ኢሕአዴግ ፖለቲካችንን ወደጨረባ ተስካርነት በለወጠበት ሁኔታ ድርጅቶችና የድርጅት ጥምረቶች ሲሰፉና ሲቀደዱ እያየን ነው፡፡ ሕዝባዊ ዓላማ ሳይኖራቸው ፍርፋሪ ይገኝ እንደሆን ተብሎ የተፈጠሩትን ትተን ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ የነበራቸውን ብቻ እንኳ ብናነሳ የሚከተለውን አጭር ግምገማ ማቅረብ ይቻላል፡፡

ግምገማችንን በኢህአዴግ ዘመን ላይ ብናቶኩር፤ የኢዲኃቅ አባል የነበረውና በኮ/ል ጐሹ ይመራ የነበረው መድኅን ከኢዲኃቅ ቀጥሎ በውጭው ዓለም አንድ ሰሞን ገኖ ነበር፡፡ አገሬ ብሎ የሚጮኸውን ሁሉ ለመጠቀም አስቦ፣ ‹‹ሁለቱንም ጭራቆች በሁለት እጆቼ እወጋለሁ›› (ደርግና ኢሕአዴግን ማለቱ ነው) ብሎ በመናገሩ ሰፊ ድጋፍ መሰብሰብን የቻለው ኮ/ል ጎሹ ብዙውም ሳይራመድ ወደቀ፡፡ ጊዜው ጀግና የሚፈለግበት ጊዜ ስለነበር፤ የኮሎኔሉ ወታደርነት ብዙው ሰው የሚፈለገው ጀግና መሪ እንደተገኘ ቆጥሮት ነበር፡፡ ኮሎኔሉ፤ የሀገሪቷ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስለነበረም የብዙ አፍሪካ

ሀገሮችን ድጋፍ እንደሚያስገኝም ታምኖበት ነበር፡፡ የተበታተነው የኢትዮጵያ ሠራዊትም ተገቢ ሰብሳቢ አግኝቷል ተብሎም ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ኮሎኔሉን በእርግጥም የኢትዮጵያ መድኅን ተድርጐ እንዲቆጠር አድርጐትም ነበር፡፡ ነገር ግን የድጋፉ ከፍታ ጊዜያዊ መሆኑን በውል ያልተገነዘበው ኮሎኔል ጎሹ የድል አድራጊነቱን ዕድል፣ ብዙ ሰው ሶሻሊዝምን አመጡብን ብሎ ከሚቃወማቸው ኢሕአፓና መኢሶን ጋር መጋራት አልፈለገም፡፡ ምናልባትም፣ የድርጅት ሥራን ከኔ ቡድን የተሻለ ይችሉበታል ብሎ ፈርቷቸውም ሊሆን ይችላል፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ መድኅን ከኢዲኃቅ ወጥቶ በኢዲኃቅ ላይ ፕሮፓጋንዳ ሲከፈት፣ ኢዲኃቅ መሽመድመድ ጀመረ፡፡ ለኢዲኃቁ መዳከም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው መድህንና ኮ/ል ጐሹም የጥሎ ማለፍ ፖለቲካቸው ሜዳ ላይ ቀረ፡፡ ይህም ደርግ ከወደቀ በኋላ በከንቱ የባከነ አንዱ ትልቅ ሙከራ ይመስለኛል፡፡

ኢዲኃቅ ለመሞት ሲያጣጥር 1986 ላይ ሌላ ግዙፍ ኅብረት ሀገር ውስጥ ተመሠረተ፡፡ ይህ የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት የሚባለው የተመሠረተው ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ በሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ስለሆነ፣ በሁለት ምክንያቶች ተስፋ ተጥሎበት ነበር፡፡ አንደኛው ምክንያት፣ ይህ ድርጅት አንጋፋ ፖለቲካ ድርጅቶችንና አዳዲሶቹንም አጣምሮ በመያዙ የተሻለ ሊንቀሳቀስ ይችላል ተብሎ ግምት በመሰጠቱ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት፣ በሀገር ውስጥና ውጭ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ኃይሎችን ስለያዘ የተሻለ ይንቀሳቀሳል የሚል ግምት በማሳደሩ ነበር፡፡ ነገር ግን ውሎ ሳያድር፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በሽታ ቀስፎ ያዘው፡፡ ከውስጥ እነመላ አማራ ሕዝብ ድርጅት አፈገፈጉ፡፡ ከውጭ፣ ኢሕአፓና መኢሶን ገሸሽ ማለት ጀመሩ፡፡ የሁለቱም ችግር የዶ/ር በየነ ጴጥሮስ አመራር አልተመቸንም የሚል እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ከ100ሺ ሕዝብ በላይ ለድጋፍ ሰልፍ ይወጣለት የነበረው አማራጭ ኃይሎች ም/ቤት የወደታች ጉዞውን ቀጠለ፡፡ የሌሎች ድርጅቶች አሰባሳቢ አካል መሆኑም ቀርቶ ራሱን ወደ አንድ ድርጅትነት ለወጠ፡፡

ለአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት መደከም ሀገር ውስጥም ሆነ ውጭ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን አጥብቀው የሚኮንኑ በስፋት እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሌም የሚከነክነኝ፣ ፕሮፌሰር በየነን የመቃወም መብታቸውን ብቀበልላቸውም፣ ከሱ የተሻለ ሥራ መሥራት ያለመቻላቸው ነው፡፡ በፖለቲካ ዓለም፣ በተለይም በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ማፍረስ በጣም ቀላል ነው፡፡ መገንባት ግን እጅግ በጣም ከባድ ነው፡፡ ለአንድ ሰው አቋም ትክክለኛነትም የተሻለ ሥራ ከመሥራት የበለጠ ምስክርነት እንደሌለም ይታወቃል፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ መሪዎች የሚጨነቁት ለሕልማቸው ሲሉ ስለሚያፈርሱት ድርጅት እንጅ በተሻለ ጠንካራ መሠረት ላይ መገንባት ስለሚችሉት ጠንካራ ድርጅት አይደለም፡፡ በነገራችን ላይ በፖለቲካ ዓለም አብሮ ለመሥራት መሠረታዊው ጉዳይ የባልና ሚስት ዓይነት ፍቅር ሳይሆን (የባልና ሚስትም ግንኙነት ፍቅር ብቻ ከሆነ እጅግ በጣም ብዙ ትዳሮች ይፈርሱ ነበር) የጋራ ሀገራዊ ጉዳዮችንና የጋራ ጥቅምን በጋራ ለማስከበር የመቻል ጉዳይ ነው፡፡ እዚህ ላይ ከባልና ሚስት የበለጠ ፍቅር ቢጨመርበት ጥሩ ነው፣ የበለጠ የተሳካ ሥራ ለመሥራት ያመቻልና፡፡ ነገር ግን ወደ መቶ ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ሀገር ፖለቲካን በወደድኩሽ፣ በጠላሁሽ ደረጃ አብሮ ለመሥራት መፈለግ ፈጽሞ እንደማይቻል የኢትዮጵያ ፖለቲካ መሪዎች

ማወቅም፣ መዋጥም ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይ ለዘመናት  በብዙ የታሪክ ቁርሾዎች የታጨቀ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዓይነቱን እየተነጋገሩና እየተደራደሩ ካልሠሩ ብዙ መንገድ መጓዝ የሚቻል አይመስለኝም፡፡ በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ እንደ ዕድል ሆኖ ፃድቃን የሚያንሱና ኃጢአተኞች የሚበዙበትም ይመስለኛል፡፡ ጻድቃን እነማን እንደሆኑ ለመለየትም በቀላሉ የሚቻል እንዳልሆነም ይታወቃል፡፡ የቡዳ ፖለቲካችን መረሳት የሌለበት ለዚህ ነው፡፡

በ1991 አካባቢ ሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ኃይሎች የተሰበሰቡበት ሌላ የተቃዋሚ ኃይሎች ኅብረት ተመሥርቶ ነበር፡፡ በፈረንሳይ ዋና ከተማ የተመሠረተው ይህ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርጅቶች ኅብረት (ኢተፓድኅ) የሚባለው ብዙም ሳይሠራና ሳይቆይ በየድርጅቶቹ ሕልሞች ግጭት በውጥረት ተፈጥሮ፣ በውጥረት የከሰመ የተቃዋሚዎች ጥምረት ነበር፡፡

ኢተፓድህ ሞቶ በውል ሳይቀበር፣ ከሀገር ውስጥና ውጭ ተቃዋሚዎችን ለማሰባሰብ ሰፊ ጥረቶች ተጀመሩ፡፡ በሀገር ውስጥ አቶ ኃይሉ በኢዴፓው ልደቱ ላይ ጠንካራ ጥርጣሬ ስለነበራቸው፣ ኢዴፓን ሳይጨመር ከሳምንታት በላይ ያልቆየ ኅብረት ተፈጠረ፡፡ የዚህ ድርጅት ውልደትም ሆነ ሞት ለብዙ ሰው ይቅርና ለብዙ ለአባሎቻችንም መታወቁን እጠራጠራለሁ፡፡ ምርጫ ቦርድ የሚባለውም ጋ ፋይሉ መድረሱንም አለሰታውሰም፡፡ ስሙ ዴሞክራሲያዊ ትብብር በኢትዮጵያ (Joint Action for Democracy in Ethiopia) ይባል እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡

በተመሳሳይ ጊዜ ተቃዋሚዎችን ለማሰባሰብ በጣም ሰፊ ሊባል የሚችል ጥረት ሲያደርግ የነበረው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ጉባኤ (ኢሀጉ) የሚባል ኢትዮጵያዊያኑ የዲያስፖራዉ ማኅበረሰብ አባላት የፈጠሩት የሲቪክ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዲኃኅ) በ1995 መጨረሻ ላይ እንድመሠረት አደረገ፡፡ በእውነቱ እስከዛ ድረስ የነበሩ ጥምረቶች ለምን እንደፈረሱ በሚገባ ጊዜ ወስደን ተነጋግረንበት ነበር፡፡ በግምገማውም ከመኢሶንና ኢህአፓ ልምዶች እስካዘን ጊዜ የተፈጠሩ አዳዲስ ፓርቲዎች ተሞክሮዎችም ተካተው ነበር፡፡ ከኦነግ በስተቀር ከሀገር ውስጥም ውጭም ያሉ ስም ያላቸው ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ተካተውበትም ነበር፡፡ ዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ያለው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብም በእልልታ ተቀበሎን ነበር፡፡ የመከፋፈል ፖለቲካችንን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዘግተን አዲስ የትብብርና የአንድነት ምዕራፍ እንደከፈትን ለሕዝቡ አብሰረንም ነበር፡፡

ሕዝቡ በታላቅ ደስታ ተቀበሎን፣ እደጉ ተመንደጉ ቢለንም በሽታችን ግን አልተለየንም፡፡ ሕዝቡ የሰጠንን የታሪክ ሠሪነት ዕድል ሳናባክን አንድ ሌሊትም እንኳ አላደርንም፡፡ ወይ ሁላችንም እንደምንለው ዴሞክራቶች አይደለንም፣ ወይ ሁሌ የሚከተለን የሕልሞቻችን ጥላ አልተለየንም፣ አዲሱ ኅብረት ከመሬት ሳይነሳ የገመድ ጉተታው ተጀመረ፡፡ የገመድ ጉተታ ፖለቲካውን በአቶ ኃይሉ የሚመራው የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ጀመረው፡፡ ውሎ አድሮ የልደቱ ኢዴፓም ተከተለው፡፡ በሥልጣን ጉዳይ ላይ ሊነሳ የሚችለውን ቅሬታ ለማስቀረት በዙር አመራር የመያዝ ቀመራችንም አልሠራ አለን፡፡ ሀገራችንን ቀስፎ ከያዛት የፖለቲካ በሽታ በቀላሉ እንደማትድንም ያወቅኩት ያኔ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡

ወደኋላ ተመልሼ ስመለከተው፣ ኅብረት ከመሬት ሳይነሳ የገጠሙት ችግሮች ከሦስት አቅጣጫዎች የመጡ ይመስለኛል፡፡ አንደኛው አቅጣጫ፣ በፖለቲካ አቋማቸው ቀኝ-ዘመም የሆኑ ኃይሎች፣ በፖለቲካ አቋማቸው ግራ-ዘመም ከነበሩት ኢህአፓና መኢሶን ጋር የታሪክ ጠባቸውን አላቆሙም፡፡ በሁለቱ ድርጅቶች ላይ ፍራቻ እንዳላቸውም ይታወቃል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ፤ ቀኝ-ዘመሞቹ የብሔር ንቅናቄዎች በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የላላ አቋም አላቸው ስለሚሉ ከነሱ ጋርም ከልብ ለመሥራት ስለሚጨንቃቸው ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ አጉል የፖለቲካ ገመድ ጉተታ ውስጥ ገባን፡፡ የዲያስፖራ ደጋፊዎችም በኢትዮጵያ ሁኔታ ድርጅቶቹ ተሸክመው መሄድ የማይችሉትን ሸክም ይጭኑባቸዋል፡፡ በዛም ሆነ፤ በዚህ የፖለቲካ ድርጅቶቹ ከመሪዎቻቸው ሕልም ያለፈ ሥራ መሥራት አልቻሉም፡፡ ሦስተኛው አቅጣጫ፣ ከኢሕአዴግ የከፋፍለህ ግዛ ሤራ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ አንድ ድርጅት ተፈጥሮ መጠናከር ሲጀምር ኢሕአዴግ የራሱን ተልእኮ አሸክሞ ወደ ድርጅቱ አሥርጎ ያስገባል፣ ወይም በድርጅቶቹ ውስጥ አሞሌ ለመላስ ፍላጐት የሚያሳዩትን ይመለምላል፡፡ አንድ ድርጅት ከእጁ የሚወጣ ከሆነ ዱላንም ይጠቀማል፡፡ ብዙውን ጊዜ ኢሕአዴግ ለተቃዋሚ አባላት፣ አሞሌና ዱላን ይዞ ይቀርባል፣ በአሞሌ ያልወደቀ በዱላ ይወድቃል፡፡ አንዱና ትልቁ የተቃዋሚ ድርጅቶች ፈተና እነዚህን መሰናክሎች ያለማለፋቸው ነው፡፡ እነዚህ ወደፊትም ቢሆን የግድ መፍትሔ ማግኘት ያለባቸው ቃላል ያልሆኑ ፈተናዎቻችን ናቸው፡፡

የቡዳ ፖለቲካችን በቀላሉ፣ ብዙም ሳይቆይ ኅብረት እንዲሰነጠቅ አደረገው፡፡ አንድ ጠንካራ ግንባር ስንል ቆይተን ሁለት ተቀናቃኝ ኅብረቶችን ወደመፍጠሩ ገባን፡፡ በአፍ የምንለው ሌላ፣ በተግባር የምንሠራው ሌላ ስለነበር፣ ዳግም ተከፋፈልንና ለኢሕአዴግ የከፋፍለህ ግዛ ሤራ ሰለባ ሆን፡፡ ዛሬ ላይ ሆኜ ስገመግመው ባንከፋፈል ኖሮ፤ ሌላው ቢቀር የ1997ቱ ምርጫን ድልና ሽንፈት ክስተት - ድላችንን የተሻለ ለማጣጣም፣ ሽንፈታችንን ደግሞ በጣም ማሳነስ እንችል ነበር የሚል ግምት አለኝ፡፡ በሀገራችን ብሂል ‹‹ሰው የዘራውን ያጭዳል›› እንደሚባለው ሁሉ የዘራነውን የመከፋፈል ፖለቲካ ውጤታችንን በተለያየ ደረጃ አጭድነው፡፡ የኢሕአዴግ የከፋፍለህ ግዛ ሤራ መለማመጃ ሆነን አረፍነው፡፡ እዚህ ላይ ማነው ተጠያቂው ለሚለው ጥያቄ፤ መልሱ ወደቡዳው ፖለቲካችን ይመልሰናል፡፡

ከ1997ቱ ምርጫ ድልና ሽንፈት በኋላ የመብት ትግላችንን ቀጥለናል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብም ከኛው ጋር መስዋእት መክፈሉንም ቀጥሏል፡፡ ሁለት ምርጫዎች ውስጥም ገብተን ወጥተናል፡፡ ከኅብረት፣ ከቅንጅት፣ ከኢሕአዴግም ልምድ ባካተተ መልኩ (የኢሕአዴግ ተሞክሮ ስል እነስዬ፤ ገብሩና ዶ/ር ነጋሦን ማለቴ ነው) መድረክን በ2001 ፈጠርን፡፡ መድረክን ስንፈጥር በሁለት መንገዶች ተስፋ ሰንቀን ነበር፡፡ አንደኛው፣ ያለፉትን ግንባሮች ስህተቶች ከሚያውቁ (የቅንጅት፤ የኅብረትና የኢሕአዴግ ልምዶች የነበራቸው ሰዎች ይዘናል) አመራር በመፍጠራችን ነበር፡፡ ሁለተኛው ደግሞ፤ ከአንድ ዓመት በላይ ጊዜ ወስደን ኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ የፖለቲካ ልዩነቶችን አበጥረን ለማየት በመቻላችን ነበር፡፡ እዚህ ላይ ሁሉም ልብ እንዲያደርግ የምፈልገው፤ 65 ገጽ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም ስናወጣ፣ እንደመሠረታዊ ልዩነት ያስቀመጥነው ሁለት ጉዳዮች ብቻ እንደነበሩ ነው፡፡ እነሱም የመሬት ጥያቄና

የፌዴራሊዝም ጥያቄ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮችን ለወደፊቱ እንከራከርባቸዋለን፣ ከልተስማማን ደግሞ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ፣ ለሕዝበ-ውሣኔ እናቀርባለን ብለንም ስለነበር በሀገራችን ታሪክ አንድ ትልቅ እርምጃ ወደፊት የሄድን መስሎኝ ነበር፡፡ የመጀመሪያው የድርጅቱ የወቅቱ ሊቀመንባር ስለነበርኩ መድረክ ከመሬት እንዲነሳ በሙሉ ልብ ለመሥራት ሀሳብም ነበረኝ፡፡

አንድ እርምጃ ወደፊት፣ ሁለት እርምጃዎች ወደኋላ በሆነው ፖለቲካችን፣ ወደፊት እንዳልተራመድን ያወቅኩኝ ከመድረክ ምሥረታ በኋላ ወደአሜሪካ የመጣሁኝ ጊዜ ነበር፡፡ በመሬት ጥያቄና በፌዴራሊዝም ጉዳይ ላይ አንድ ካልሆናችሁ ምኑን መድረክ ፈጠራችሁ የሚለው አባባል በየሄድኩበት ሲገጥመኝ ነበር፡፡ አንዳዶቹ ከዛም አልፈው በየነንና መረራን ሥልጣን ላይ ለመውጣት ብቻ ነው የሚጠቅመው ብለው የጻፉ ነበሩ፡፡ የበለጠ የሚገርመው ደግሞ እነስዬን ወደ ሥልጣን ለመመለስ የታቀደ ነው ብለው የሚጽፉም መኖራቸው ነው፡፡ ‹‹አንድነትን አጀንዳውን ገደላችሁበት፣ አንድነት በጎሳ ድርጅቶች ተወጠ›› የሚሉ ድምጾችም ነበሩ፡፡ ለአንድነት እንጂ ለመድረክ ገንዘብ ማዋጣት የለብንም ብለው አድማ ያስመቱም ነበሩ፡፡ የውስጥና የውጭ ግፊትን መቋቋም ያቃታቸው የአንድነት መሪዎች አንድነትን ወደጠርዝ ወሰዱት፡፡ በረጃጅም ሥውር እጆቹ አንድነትን ሲቆጣጠር የነበረው ኢሕአዴግም በመጨረሻ ላይ ብቻውን አስቀርቶ የመበተን እርምጃ ሊወስድበት ችሎዋል፡፡

ዛሬ የሀገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች/ለውጥ ፈላጊ ኃይሎች በሀገር ውስጥም ሆነ ውጭ የተበታተነ አጀንዳና የትግል እስትራቴጂዎችን ይዘው እየኳተኑ ነው፡፡ ሀገር ውስጥ ኢሕአዴግ በቀጥታ የማይቆጣጠራቸው መድረክና ሰማያዊ ፓርቲ አሉ፡፡ እነሱም ቢሆኑ፣ ከኢሕአዴግ ሥውር እጆች ነጻ ይሁኑ፣ አይሁኑ የተቀናጀ ትግል ሲያካሂዱ አይታይም፡፡ ትግሉ በተሻለ ሁኔታ እንዲቀጥል ከተፈለገ ሁለቱም አንድ ዓይነት የትብብር መሥመር ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

ከሀገር ውጭ ትጥቅ ትግልን የሚያራምዱና የማያራምዱ ኃይሎች አሉ፡፡ ለምሣሌ፣ ሽንጐ የተሰኘው ስብስብ ሰላማዊ ትግል የሚባለውን የትግል ስልት የሚከተል ቢመስልም፣ ሀገር ውስጥ ካሉት ድርጅቶች ጋር የረባ ትብብር የለውም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን የትግል እስትራቴጂ ካልቀየሰ ደግሞ በምን ዓይነት መንገድ ለሰላማዊ ትግሉ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ እየገባኝ አይደለም፡፡ እነግንቦት ሰባት የትጥቅ ትግልን የሚጨምር ሁለገብ ትግል እያሉ ነው፡፡ ነገር ግን፣ ተመሳሳይ የትጥቅ ትግል እስትራቴጂ እንደሚከተሉ ከሚታወቁ ኦነግና ኦብነግ ጋር ባለኝ መረጃ የቀረበ ግንኙነት የላቸውም፡፡ በዲያስፖራዉ ዓለም ከሚንቀሳቀሰው ሽንጐ ጋርም ትብብር ያላቸው አይመስልም፡፡ ዙሪያችንን አትኩሮ ለተመለከተ ሰው የሀገራችን ተቃዋሚ ኃይሎችና ትግላቸው በመንታ መንገድ ላይ ቅርቃር ውስጥ የገባ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በፖለቲካው ዓለም መንታ መንገድ ላይ መሆን ጥሩ አይደለም፡፡ መንታ መንገድ ላይ እይታ የጠፋበት ሰው ትክክለኛውን መንገድ መልሶ ለማግኘት በጣም እንደሚቸገር ይታወቃል፡፡ ፈረንጆች መንታ መንገድ ላይ የጠፋ ሕጻን (a lost child on a cross-road) እንሁን የሚሉት ለዚህ ነው፡፡ እነሱ እንደሚሉት መንታ መንገድ ላይ የጠፋ ሕጻን፣ ወደፊት እንዳይሄድ፣ ወዴት እንደሚሄድ በትክክል አያውቅም፣ ወደኋላ እንዳይመለስ በትክክል ከየት እንደመጣ ስለማያውቅ እዛው ሲዞር ይውላል ነው፡፡

*የሀገራችን ፖለቲካ ኃይሎችም መንታ መንገድ ላይ መንገድ ከጠፋባቸው ውለው እንዳደሩ ላለፉት አርባ ዓመታት ያለፍንባቸው የፖለቲካችን ምስቅልቅል ጉዞ ከበቂ በላይ ማስረጃችን ነው፡፡*

*ከምርጫ 2007 በኋላ፣ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ነውር የሚባልን ነገር ከቁብ ሳይቆጥሩ፣ መቶ በመቶ አሸንፈናል ማለታቸው ያስደነገጣቸው ዜጎች፣ ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ፣ ከምሁር እስከ አርሶ አደር በሚያሰለች መንገድ ወዴት እየሄድን ነው? ምን እናድርግ? የሚሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁኛል፡፡ የኔም የተለመደ መልስ፣ መብትና ክብሩን ለማስጠበቅ የሚችል ሕዝብ፣ ለድምጹ ዘብ መቆም የሚችል ሕዝብ፣ የኮሮጆ ቀማኞችን መቆጣጠር የሚችል ሕዝብ ማደራጀት አለብን ነው፡፡ መደራጀት ብቻውን የሕዝብን መብት እንደማያስከብር አያጠያይቅም፡፡ የተደራጀ ሕዝብ ውጤት ለማምጣት የሚፈልገውን የሚውቅና ወዴት እንደሚመራ በሚያውቅ ኃይል መመራት አለበት፡፡ በኢትዮጵያችን እንዲህ ዓይነቱ ኃይል የተባበረ ኃይል መሆን ያለበት ይመስለኛል፡፡ ላለፉት አርባ ዓመታት የተበታተነ ትግላችን ከበቂ በላይ መስዋእትነት ቢከፈልበትም የምንፈልገውን ሕዝባዊ ድል ያላገኘነው የሞኝ ሩጫችንን ማቆም ስላልቻልን ነው፡፡ ከዚህ መውጣት የሚቻለው ደግሞ የሚከተሉትን ነገሮች በውል ስናጤንና በቁርጠኝነት ወደመፍትሔው ስንሄድ ነው፡፡*

*ከሕልም ዓለም ሳንወጣና የሚጋጩ ሕልሞቻችንን ይዘን የፖለቲካ ጉዟችንን ቀጠልን፡፡ ጨርሶ ቅርጫ እንኳ የማይመስሉ ምርጫዎች ውስጥ ገብተን ወጣን፡፡ በፖለቲካ አካሄዳችን መሠረታዊ ለውጥ ካላመጣን፣ ይኸው ሁኔታ የሚቀጥል ይመስለኛል፡፡ ከኢሕአዴጎች መጫወቻነትም የምንወጣ አይመስለኝም፡፡ ለቡዳ ፖለቲካችን መድኃኒት ፈልገን፣ መሐል መንገድ ላይ በመሰብሰብ የሕዝቦቻችንን የጋራ ትግል በጋራ ካልመራን፣ በሕልሞቻችን ዓለም ውስጥ ቀጥለን ስንዋኘ ከመኖር ያለፈ ሥራ እንደማንሠራ ያለፈው የአርባ ዓመታት፣ ወይም የሃያ አምስት ዓመታት የትግል ታሪካችን በማያሻማ መንገድ አረጋግጦልናል፡፡ ሁላችንም ከሕልሙ ዓለም ወጥተን በእውኑ ዓለም በውል ካልታገልን ለሕዝባችን የምንመኘው ውጤት የሚመጣ አይመስለኝም፡፡ እዚህ ላይ የኢሕአዴግ ቀለብተኛ ላልሆኑ የተቃዋሚ ኃይሎች አሥምሬ ማስረደት የምፈልገው፣ ለሕዝቡ ሆነ ለራሳቸው መብትና ክብር፣ ለመታገል የቆረጡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወጣቶች አሉ፡፡ የኦሮሞ ወጣቶች ያረጋገጡልን ይህንኑ ሐቅ ነው፡፡ የተባበረ ትግል ውስጥ መግበት ብንችል ኖሮ ሕዝባዊ ትግሉ ምን ያክል ወደፊት እንደሚገፉ መገመትም አያስቸግርም፡፡ እዚህ ላይ መልእክቴ የየድርጅት መሪዎች የማይሳካ ሕልሞቻችሁን ለማሳካት ብላችሁ ይህንን ወጣት ከንቱ መስዋእትነት አታስከፍሉ ነው፡፡ ብቸኛው የነፃነት መንገድ የቡዳ ፖለቲካችንን በማቆም፣ ለተባበረ የጋራ ሕዝባዊ ትግል መሰለፍ መሆኑን ለአንድ አፍታ እንኳ መዘንጋት እንደሌለብን ነው፡፡ በፍጥነት ወደዚህ ከገባንና በቁርጠኝነት ከታገልን የሕዝባችን የድል ቀንም ሩቅ አይሆንም፡፡ ከመንታ መንገድ ወደ ነፃነት መንገድ መውጫም ይኸው ይመስለኛል፡፡*

*ብዙ ጊዜ በዛ አቅጣጫ ባናስብም፣ ለፖለቲካችን መበታተን እስካሁን ድረስ በፖለቲካ መሪዎች ደረጃም ሆነ በፖለቲካ ሊቃውንት ደረጃ ከራሳቸው ማኅበረሰብ አልፈው በሀገር ደረጃ ሰፊ ተቀባይነት ያላቸውን መፍጠር ባለመቻላችን ይመስለኛል፡፡ የሌሎች ሀገሮች ታሪኮችን ስናይ፣ አሜሪካኖች እነጆርጅ ዋሽንግተንና አብርሃም ሊንከን*

የመሰሉ መሪዎች ነበራቸው፡፡ እንግሊዞች እነጆን ሎክና ሆብስ የመሰሉ የፖለቲካ ሊቃውንት ነበራቸው፡፡ ፈራንሳዎች እነሩሶን የመሰሉ የፖልቲካ ሊቃውንት ነበራቸው፡፡ ራሽያኖች እነሌኒን ነበሯቸው፡፡ በቻይና ማኦ እንደቀድሞው ባይመለክም፤ እስካሁን ድረስ ይከበራል፡፡ አፍሪካ ውስጥ ከማንዴላ፣ ምናልባት የግብፁ ናስር፤ የጋናው ንክሩማህ፣ የታንዛኒያው ኔሬሬ በስተቀር የራሳቸውን ሰፊውን ትውልድም ሆነ ከራሳቸው ትውልድ በላይ ተሰሚነት ያላቸው መሪዎች ወይም አቅጣጫ ሊያስይዙ የሚችሉ የፖለቲካ ሊቃውንት መፍጠር አልተቻለም፡፡ ሶሻሊዝምን የተሸለ ዕድል ቢገጥመው ኖሮ፤ ምናልባት የሞዛቢኩ ሳሞራ ማሼል፤ የጊኒ ቢሳዎ አሚርካል ካብራል፤ የግብፁ ሳሚር አሚንና የታንዛኒያው አብዱራህማን ባቡ በሀሳብ አመንጭነት ተቀባይነት ሊያገኙ ይችሉ ነበር፡፡

ወደ ኢትዮጵያችን ስንመጣ፣ በሀገር መሪነት ደረጃም ይሁን በምሁር ደረጃ፣ ሀገራችን ያፈራቻቸው ሰዎች ከራሳቸው ማኅበረሰብ ክልል አልፎ ያላቸው ተቀባይነትና ተሰሚነት ውሱን መሆኑ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ በሐቅ እንናገር ከተባለ፣ በስፋት የሚታወቁ የኢትዮጵያ ንጉሦች፣ ቴዎድሮስ፣ ምኒልክና ኃይለ ሥላሴ በተለያዩ ደረጃ አማራ ከሚባለው ማኅበረሰብ አካባቢ ድጋፍ ቢኖራቸውም፣ በሌሎች አካባቢዎች ያላቸው ተቀባይነት አናሳ መሆኑ ይታወቃል፡፡ እንደውም ከሁሉም በላይ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ፈጥረዋል የሚባሉት ምኒልክ በኦሮሞዎች፣ በሱማሌዎች ወ.ዘ.ተ. እንደወራሪ እንደሚታዩ የሚያከራክር አይመስለኝም፡፡ በትግራይና ኤርትራ አካባቢም የተሻለ ተቀባይነት እንደሌላቸው እሙን ነው፡፡ አፄ ዮሐንስም ተቀባይነታቸው ከትግራይ ወሰን ክልል ማለፉ አጠራጣሪ ነው፡፡ ከሁሉም ንጉሦች የተሻለ ጊዜና ዕድል የነበራቸው አፄ ኃይለ ሥላሴ እንኳን ታሪክ የሰጣቸውን እድል አልተጠቀሙም፡፡ ሌላው ቢቀር በዘመናቸው ስመጥር ከነበሩ አርበኞች እንኳ ተቀባይነት አልነበራቸውም፡፡ በላይ ዘለቀና ደጃዝማች ታከለ፣ ከጣሊያኖች ጥይት ተርፈው የሞቱት በአፄው እጅ ነበር፡፡ ኮ/ል መንግሥቱንም በሚመለከት ዋናው ጥያቄ በየትኛው ማኅበረሰብ ይደገፋል ሳይሆን፣ በሱ የጭፍጨፋ ዘመን ያልተነካው ማነው? ነው የሚል ይመሰለኛል፡፡

ኢሕአዴግ ታላቁ መሪያችን ብሎ ብዙ ከበሮ የሚመታለት አቶ መለስ ታላቅነቱም ሆነ ውርሱ ከአንድ ማኅበረሰብም ሆነ ድርጅት የማለፍ ዋስትናው እየታየኝ አይደለም፡፡ በሱ ስም ያለው ፋውንዴሽንም ሆነ በየቦታው የሚከለሉ ፓርኮች ኢሕአዴግ በዘላለማዊነት ኢትዮጵያን ይገዛል ካልተባለ በስተቀር፣ ኢሕአዴግ ሥልጣን ለቆ ከአንድ ቀን በለይ ይቆያል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ኢህአዴግ በሕይወት እያለም የኦሮሞ ሕዝብ ዐመጽ ኢላማ መሆኑ ይህንኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በተለይ ኢሕአዴግ በሰላማዊ ምርጫ ሥልጣን ካልተጋራ ወይም ካልለቀቀ የኢሕአዴግ ውርስ የሚባሉ ነገሮች የትኞቹ በእርግጥም ውርስ እንደሚሆኑ እግዜር ይወቀው ከማለት ውጭ ማሰብ ያስቸግራል፡፡

ከፖለቲካ ድርጅቶቻችንም፣ በኔ ግምት ከመኢሶን ኃይሌ ፊዳ፣ ከኢህአፓ፣ ብርሃነ መስቀል ረዳ የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ወጣት ድጋፍ ለማግኘት ከሌሎቹ የተሻለ ዕድል ነበራቸው፡፡ የሁለቱም ድርጅቶች ገና በጨቅላ ዕድሜያቸው ስለተዳከሙ ዕድሉን በቀላሉ አጥተዋል፡፡ ከዚያም በላይ፤ ኃይሌ ፊዳ ከተፈጠረበት የኦሮሞ ማኅበረሰብ ዛሬ ያለው ተቀባይነት በጣም አናሳ ሲሆን፣ ብርሃነ መስቀል ረዳ ደግሞ

በኢህአፓ ደረጃ እንኳን እንዳ ከሀዲ የሚቆጥሩት ብዙ ናቸው፡፡ በዛም ሆነ በዚህ፣ ሁለቱም ቢሆኑ በኢትዮጵያ ደረጃ እንኳ በእነፋኖንና ቼኩቬራ ደረጀ ለመታዬት ዕድል አላገኙም፡፡ በመፈንቅለ መንግሥት ለውጥ ለመምጣት የሞከሩ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ (ከአማራ አከባቢ ያለፈ) ጄኔራል ታደሰ ብሩ (ከኦሮሞ አከባቢ ያለፈ) ተቀባይነት ያላቸው አይመስለኝም፡፡ በምሁራን በኩልም ያለን ችግር የተሻለ አይደለም፡፡ በእነሎክና ሩሶ ደረጃ የሚታዩ ይቅርና በሀገራችን ደረጃ እንኳ ከራሳቸው ማኅበረሰብ አልፈው ተቀበይነት ያላቸውን ማግኘት ያስቸግራል፡፡ በተለይ በምሁር ግዙፍነታቸው ሰፊውን የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ የፖለቲካ አቅጣጫ ማስያዝ የቻሉ እስካሁን የሉንም ወይም ሀገራችን እንደዛ ዓይነት ቁመና ያላቸውን ሰዎች መፍጠር አልቻለችም፡፡ ወይንም ደግሞ በዛ ደረጃ ለመታየት የሚችሉ የላትም፡፡ የሁለቱም ውጤት ግን አንድ ነው፡፡

- *መደምደሚያ፣ የቡዳ ፖለቲካችንና ሕልሞቻችን ሊታራቁ ወይስ ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ?*

የሀገራችን ፖለቲካ ወደ መንታ መንገድ ሲገፋ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም፡፡ በተደጋጋሚ ብዙ መንታ መንገዶች ውስጥ አልፏል፡፡ በኔ እይታ ቢያንስ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ፣ የአፄው መንግሥት መውረድ፣ የደርግ ሥልጣን ላይ መውጣት፣ የደርግ፣ የመኢሶንና የኢሕአፓ የሦስትዮሽ ፍጥጫ፣ የደርግ ድል መመታትና የሕወሐት ሥልጣን ላይ መውጣት፣ የ1997ቱ ምርጫ በአንድ ትውልድ ዘመን ያለፍናቸው መንታ መንገዶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወዴት? የሚል መሠረታዊ ጥያቄ ያስነሱ ክስተቶች ነበሩ፡፡ የሀገራችን ፖለቲካ ጉዞ አቅጣጫውን ያጠንበት ጊዜያትም ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ ልብ ማድረግ የሚያስፈልገው፣ የእነዚህ መንታ መንገዶች ፖለቲካ ጊዜያዊ አሸናፊዎች በጊዜያዊ ድል እንዲኩራሩ ሆኗል፡፡ ነገር ግን ድሎቻቸው ከጊዜያዊነት አላለፉም፡፡ ለአሸናፊዎቹ እንኳ እስካሁን ከጊዜያዊ የፖለቲካ ስካር አልፎ ዘላቂ ድል አልሆኑላቸውም፡፡ በተለይ ለሀገሪቷ መሠረታዊ ለውጥ አላመጡም፡፡ አንዳንዶቹ የእንቧይ ካብ ነበሩ ለማለትም ይቻላል፡፡

ከ1960ዎቹ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሀገራችን በፖለቲካ ቀውስ ውስጥ የምትዳክረው፣ ጊዜያዊ ድል አድራጊዎቹ ከሁለት ነገሮች አንዱን ማድረግ በለመቻለው ነው፡፡ ወይ በጊዜያዊ ድላቸው የፖለቲካ ስካር ውስጥ ከመግባት እራሳቸውን ጠብቀው፣ ድሉን ለሀገሪቷም ሆነ ለሕዝቦቿ የጋራ ድል ማድረግ አልቻሉም ወይ ደግሞ በራሳቸው ደረጃ ወደ ዘላቂ ድል መውሰድ አልቻሉም፡፡ የበለጠ ግልጽ ላድርግ፡፡ ለምሳሌ፣ የደርግ መንግሥት ‹‹ተፈጥሮን በቁጥጥር ሥር እናደርጋለን›› ከሚል መፈክር ጀምሮ ስለገባውም ስላልገባውም መፈክር ለ17 ዓመታት ባዶ ጫጫታ ሲያሰማ ከርሞ ሀገሪቷንና ሕዝቦቿን ለባለጊዜው አምባገናን ያለደረሰኝ አስረክቦ ሄደ፡፡ እርግጠኛ ነኝ፣ የደርግ ባለሥልጣናት በአደባባይ ባያምኑም፣ (አንዱ የቡዳ ፖለቲካ ችግሩ ይሄ ነው) በልባቸው በድንቁርና ስለፈጁዋቸው የሀገሪቱ ወጣቶች የሚገነዘቡ ይመስለኛል፡፡ አንዳንዶቹ በማያውቁት አይዶሎጂ የአንድ ትውልድ ምርጥ ወጣቶችን ቢፈጁበትም፣

እግዜር አለ ብለው ሲጸልዩ እሥር ቤት መክረማቸውና በሃይማኖት መሪዎች አማላጅነት መፈታታቸው ስለማያውቁት ነገር ሲሡሩ እንደከረሙ የሚያሳይ አንዱ ምልክት ነው፡፡ የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ባለሳምንት የሆነው ኢሕአዴግም፣ የደርግ ተመሳሳይ ዕድል ይግጠመው፤ አይግጠመው ለወደፊቱ ታሪክ ብንተውም፤ አሁን ባለው ሁኔታ በሚሡራቸው ሥራዎች ውስጥ ከደርግ ያላነሱ ባዶ የመፈክር ጫጫታዎች እንደሚበዙበት እያየን ነው፡፡ ሕልሞቹ ቢያንስ፤ የኢትዮጵያውያን የጋራ ሕልም መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ብዙ ነገሮች የሉብትም፡፡ ከዚህ አኳያ ቢያንስ ከኢሕአዴግ ደጋፊዎች ውጭ ለኢሕአዴግ ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ በጣም ጥቂቶች ይመስሉኛል፡፡ ሌላው ቢቀር የኢሕአዴግ መንግሥት ሠራሁኝ ለሚላቸውም ምሥጋና ያጣ መንግሥት ነው ለማለት ይቻላል፡፡

የኢሕአዴግ ሕልም እንዳይሳካ የሚያደርጉ ብዙ ምክንያቶችን መዘርዘር የሚቻል ይመስለኛል፡፡ አንደኛውና ዋናው ምክንያት፣ በኤርትራውያን ድጋፍም ቢሆን ኢሕአዴግ በደርግ ላይ ያገኘውን አንፀባራቂ ሊባልለት የሚችለውን ወታደራዊ ድሉን ወደ ፖለቲካዊ ድል መለወጥ ያለመቻሉ ነው፡፡ ያንን ለመደበቅ ደግሞ ሁሌም የሕዝብ ድምጽ እያጭበረበረ መኖር ውስጥ ገባ፡፡ ዘላለም የሕዝብ ድምጽ እያጭበረበሩ መኖር ደግሞ ያስቸግራል፡፡ ሁለተኛው ችግሩ፣ ኢሕአዴግ የደርግ መንግሥትን አሸነፈ እንጅ፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብን ወይም ተቀናቃኙ ሊሆን የሚችሉ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የደቡብ የአትዮጵያ ሕዝቦች፣ ወዘተ ልሂቃንን አይደለም፡፡ በ1997ቱ ምርጫ ኢሕአዴግ ከነዚህ ሕዝቦች በወጡት ልሂቃን በቀላሉ ተሸንፎዋል፡፡ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ትልቁ ችግር ላለፉት 25 ዓመታት ሳይረዱ ወይም መረዳት ሳይፈልጉ ቀርተው ደርግን ማሸነፋቸውን ሲያወሩ መኖራቸው ነው፡፡ የደርግን መንግሥት እንደ መንግሥት ማሸነፍ ሌላ ጨዋታ ነው፣ የተሻለ የሕዝብ ድጋፍ አለን የሚሉትን ተቀናቃኞችን ማሸነፍ ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን እውነታ የኢሕአዴግ መሪዎች ቢረዱ ሀገሪቷንና ሕዝቦቿን ከአጉል አጥፍቶ መጥፋት ፖለቲካ ያድናሉ የሚል ግምት አለኝ፡፡ ሦስተኛው፤ ኢሕአዴግ ከየአካባቢው ሕዝቦች እየመለመለ በፖለቲካ ድርጅትነት ጠፍጥፎ የሚያሠማራቸው የጠበቀውን ያህል ሕዝባዊ ድጋፍ እያመጡለት እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ዘሬ ኦፒዲኦና/ኢህአዴግን ኦሮሚያ ውስጥ እየገጠማቸው ያለው ሰፊ ተቃውሞ በግልጽ የሚያሰው ይህኑን ነው፡፡ ይህ ለኢሕአዴግ መሪዎችም የመንቂያ ደወል ይመስለኛል፡፡ አራተኛው፣ ኢሕአዴግ ወታደራዊ ድሉን በደርግ ላይ ያገኘው በኤርትራው ግንባር ድጋፍ ጭምር መሆኑ ይታወቃል፡፡ የትግራይ ተወላጅ የሆነው ታሪክ ፀሐፊ፣ ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ በትክክል እንዳስቀመጠው፣ ሕወሐት ያለሻዕቢያ እርዳታ ደርግን አሸንፎ ምኒልክ ቤተመንግሥት ይገባል ማለት የማይተሰብ ይመስለኛል፡፡ ኢሕአዴግ የሻዕቢያን አጋርነት ማጣት ብቻ ሳይሆን፤ ቋሚ ጠላት ማድረጉ ለኢሕአዴግ ትልቅ ኪሣራ ነው። ይህም ላለፉት አሥራ ስምንት ዓመታት ለኢሕአዴግ መሪዎች ትልቅ ፈተና እንደነበረ ይታወቃል፡፡ የኢሕአዴግ መሪዎች፣ ሁሌም ‹‹እኛው እንሻላቸዋለን፣ እንታረቅ›› የሚል ጥሪያቸው ከዚሁ እውነታ የመነጨ ይመስለኛል፡፡ መሬት ሰጥተው እንዳይታረቁ ደግሞ በተላይ የትግራይን ሕዝብ እንደፈሩ አጠራጣሪ ጉዳይ አይደለም፡፡

አምስተኛው፤ ችግራቸው (ተቸግረውም ሊሆን ይችላል) በሶማሊያ ውስጥ ዘሎ መግባት ነው፡፡ ኢሕአዴግ አሜሪካኖችን ለማስደሰት ይሁን፤ ለራሱ የፖለቲካ ጨዋታ (ሁለቱም ሊሆኑ ይችላሉ) ከገባበት የሶማሊያው ጨዋታው በቀላሉ ሊወጣ ይችላል የሚል ግምት የለኝም፡፡ አሜሪካ እንኳ በዓለም ላይ የለቀ ሀብት፤ ቴክኖሎጅና ሰራዊት ይዛ ኢራቅና አፍጋኒስታን ገብታ መውጫው እንዳጠራት እያየን ነው፡፡ የኢትዮጵያችን ምን

ሊመስል እንዳሚችል መገመት አያስቸግርም፤፤ ስድስተኛ፣ ኢሕአዴግ ለፈረንጆች ፍርፋሪ ብሎ በአንድ በኩል፣ የብዙሃን ዴሞክራሲ፣ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ፤ ነፃ ገበያ፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ወ.ዘ.ተ. አሰፍናለሁ ይላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከነዚህ በፍጹም ተፃራሪ የሆነ፤ የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ ሥርዓትን ለመገንባት ይጥራል፡፡ ሁለቱንም ፍጹም ተጻራሪ የሆኑ ነገሮችን አብሮ ለማስኬድ ለማንም ከባድ ነው፡፡ ይህ በዴሞክራሲ ስም የአውራ ፓርቲ (ልጆች ሲቀልዱ አውሬ ፓርቲ ይሉታል) ግንባታ ሕልም በቀላሉ ለኢሕአዴግ የሚሳካ አይመስለኝም፡፡ ላለፉት 24 ዓመታት ትልቁ የኢሕአዴግ መሪዎች ፈተና ይኸው ይመስለኛል፡፡ የኢሕአዴግ መሪዎች ለራሳቸውም ሲሉ አንዱን መምረጥ የሚኖርባቸውም ይመስለኛል፡፡ በእነዚህ ዓይነቱ የማስመሰል ፖለቲካ ሕዝብን እያመሱ መኖር ሁላችንንም ውድ ዋጋ እንዳያስከፍለንም ትልቅ ሥጋት አለኝ፡፡ ሰባተኛው፣ ኢሕአዴግ ፌዴራሊዝም ብሎ ዴሞክራሲ-አልባ የሆነ የሞግዚት አስተዳደር ለመፍጠር የሚያደርገው መዳከር ብዙ ቦታዎች የችግሮች ምንጭ እየሆነበት መጥተዋል፡፡ የኢሕአዴግ መሪዎች የፈለጉትን መከራከሪያ ቢደራድሩም፤ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዴሞክራሲ-አልባ የሆነ ፌዴራሊዝምን ማሰብ ከአስቸጋሪነት በላይ ነው፡፡ ኢሕአዴግ የገፋበትን መንገድ ደጋግሞ ቢያስብበት የሚጠቅመው ይመስለኛል፡፡ በውሸት ላይ የተገነባ ነገር ውሎ፤ አድሮ መፍረሱ አይቀርም፡፡ አንዳንድ የኛ ልጆች ሕወሐት ኦሮሚያ ውስጥ እየዘረጋ ስላለው መዋቅር ሲናገሩ፣ ‹‹በአህያ ቆዳ የተሠራ ቤት፣ ቤት ሆኖ የሚቆየው ጅብ መጥቶ እስከሚጮህበት ጊዜ ነው›› የሚሉት እውነትነት አለው፡፡ እኔም ይህንን አባባል እጋራለሁ፡፡ ኢሕአዴግ ጠመንጃውን ከጨዋታው ካወጣ፣ ኦህዴድ እንደፖለቲካ ፓርቲ 24 ዓመታት መቆየት ይቅርና ለ24 ሰዓታት የኦሮሞ ሕዝብ ውስጥ መቆየቱ ያጠራጥረኛል፡፡ በአጭሩ፣ የራሳቸው ሕይወት የሌላቸውን የሞግዚት አስተዳደሮች በሕዝብ ላይ ጭኖ፣ ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ልጆች እያስተዳደሩ ነው ብሎ መቀለድ አስቸጋሪም፣ አስነዋሪም ይመስለኛል፡፡ የውሸት ፌዴራሊዝሟ ጉዳይ ለሀገሪቷ ትልቅ አደጋም አለት፡፡ ነፍሳቸውን ይማርና ሶቪዬት ኅብራትና ዩጎስላቪያ በዋናናት የፈረሱት በውሸት ፌዴራሊዝምና በውሸት ምርጫ ምክንያት መሆናቸው መርሳት የለበትም፡፡

ስምንተኛው፤ ችግር ሀገሪቷ ‹‹በሁለት አሀዝ እያደገች ነው፤ በልማትና ብልፅግና ጐዳና እየገሠገሠች ነው፣ በአሥር ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እናስገባታለን፣ ተአምር እየተሠራ ነው›› ወ.ዘ.ተ. የሚባሉ ቀልዶች ብዙ የሚያስኬዱ አይደለም፡፡ ሕዝባችን ሲተርት፣ ‹‹እየዋሹ ያለፉበት መንገድ፤ መመለሻው ላይ ያስቸግራል›› የሚለው እንዲህ ዓይነቱን ነው፡፡ ጥቂት የኢሕአዴግ ሚሊየነሮች እየተፈጠሩ መሆናቸው ቢታወቅም፣ ሚሊዮኖች እየተራቡ እንደሂዱና ከፈረንጅ በሚገኘው ምጽዋት እንደሚኖሩ ይታወቃል፡፡ በ8 ሚሊዮን ብር በሚገዙ መኪኖች የሚነሸነሹ እንዳሉ፤ ሚሊዮኖች በበዶ እግራቸው እንደሚኳትኑ ይታወቃል፡፡ ይህንን እውነታ ለመረዳት ጠዋትና ማታ አዲስ አበባ ከተማ ዙሮ በታክሲዎችና በአውቶቡስ ጣቢያዎች የሚጋፋውን ሕብረተሰብ ከባለሚሊዮን መኪና ቅንጡዎች ጋር ማወዳደር በቂ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮችን በትዝብት ብቻ ማለፉ ያስቸግራል፡፡

በግልጽ እንነጋገር ከተባለ፣ በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እንገባለን ተብሎ ከበሮ ይመታል፡፡ ነገር ግን በዓለም ደረጃ በሚወጡ መረጃዎች ኢትዮጵያችን አሁንም የዓለም ጭራ ከሆኑት ሀገሮች ተርታ ናት፡፡

ከሁሉም በላይ ለዚህ ምስክር ሊሆነን የሚችለው ደግሞ ሀገራችን ተስፋ ያጡ ወጣቶች የሚሰደዱበትና በደቡብ አፍሪካ ከነመኖሪያ ቤታቸው የተቃጠሉበት፤ በሊቢያ በረሃ የታረዱበት፣ በቀይ ባሕር፤ ሕንድ ውቅያኖስና የሜዲቴሪያንያን ባሕር የውሃ ሲሳይ የሆኑባት ሀገር ናት፡፡ የኢሕአዴግ በለሥልጣናት ጠዋትና ማታ ልማትና ብልፅግና የሚሉን፤ ወደነሱ የተጠጉ ቅንጡዎችንና ካድሬዎቻቸውን ስለሆነ እጅጉን እንደተሳሳቱ ሊነገራቸው ይገባል፡፡ ‹‹ሕዝባዊ አደራ›› ብሎ፣ ሕዝብን ማጭበርበር በምድርም፣ በሰማይም እንደማያፀድቃቸውም ሊነገራቸው ይገባል፡፡ የኢሕአዴግ መሪዎች ሚሊዮኖችን እያስራቡ በሕዝብ እንባ መቀለድ ምን ጊዜም እንደማይረሳና እንደሚያስጠይቅም ማወቅ ይገባቸዋል፡፡

ኢሕአዴግ ዘላቂ ሰላምና ብልጽግናን ለሁሉም ዜጎች ሊያመጣ የሚችለው እላይ ያነሳናቸውን መንታ መንገዶችን ሲሻገርና ሕዝቡንም ሲያሻግር ነው፡፡ እንቆቅልሹ ግን ኢሕአዴግ እነዚህን መንታ መንገዶችን ከተሻገራቸው ደግሞ ኢሕአዴግነቱ ይቀራል፡፡ የኢሕአዴግ መሪዎችም ሁለት ወዶ ሆኖባቸው ነው እንጂ እንቆቅልሹን የሚያውቁት ይመስለኛል፡፡ ካላወቁ ደግሞ የሊቢያው ጋዳፊ የሞት አፋፍ ላይ ሆነው ‹‹የሊቢያ ሕዝብ በጣም ይወደኛል›› የሚለው ዓይነት ቅዠት ነው የሚሆነው፡፡ በነገራችን ላይ ማንም ሰው ሆነ መንግሥት በጤናማ አእምሮው መጥፎ ለመሆን የሚያስብና የሚፈልግ የለም፡፡ ዋናው ጉዳይ ጥሩ ሥራ መሥራት መቻልና ያለመቻል ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም፤ ኢሕአዴግ ከገባበት የፖለቲካ ቅርቃር ውስጥ በቀላሉ ለመውጣት የሚቻለው አይመስለኝም፡፡ አንድ እርምጃ ወደፊት፣ ሁለት እርምጃዎች ወደኋላ የሆነው የኢሕአዴግ ጉዞም፣ በዚሁ ምክንያት ይመስለኛል፡፡ የሁለት ወዶ ፖለቲካ ውጤት ሁሌም ከዚህ እንደማያልፍ ይታወቃል፡፡ ሥዩመ እግዚአብሔር ነኝ ይሉ የነበሩት ንጉሥና የደርግም ችግር ይኸው ነበር፡፡ በአንድ በኩል ፈላጭ ቆራጭ ሥልጣናቸው እያጓጓቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለሕዝብ ልማትና ብልጽግና እየሠራን ነው ሲሉ ቀኑ እየመሸባቸው ነው ወደ ውርደቱ ዓለም የገቡት፡፡ ደጋግሜ እንደምለው፣ ፖለቲካ በአጣቃላይና የሀገራችን ፖለቲካ እስከገባኝ ድረስ፤ የሀገራችን ፖለቲካ ከገባበት ቅርቃር ውስጥ የሚወጣው ወይ እኛ ኢሕአዴግን ከገባበት ቅርቃር ለማስወጣት የሚያስችል የተባበረ ትግል ውስጥ በቁርጠኝነት መግባት አለብን፣ ወይ የኢሕአዴግ መሪዎች ከንጉሡም፣ ከደርግም ተምረው ከሌሎች ኃይሎች ጋር ብሔራዊ መግባባት ፈጥረው ሀገሪቷንና ሕዝቦቿን ለመታደግ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ሲያሳዩ ነው፡፡

ተቃዋሚዎችም ልብ እንዲያደርጉልኝ የምፈልገው፤ እነሱም እንደ ኢሕአዴግ የፖለቲካ ቅርቃር ውስጥ መግበታቸውን በውል ተገንዝበው፤ ከገቡበት የፖለቲካ ቅርቃር ውስጥ ለመውጣት በቁርጠኝነት መሥራት እንዳለባቸው ነው፡፡ እላይ እንዳነሳሁኝ፤ እራሳችንም ሁሌ የፖለቲካ ቅርቃር ውስጥ እየዳከርን፣ ሥልጣንን እንደልቡ የሚጠቀምበት፤ የሕዝብን ሀብትና ንብረትን እንደፈለገው የሚጫወትበትና እንደፈለገው የሚያዝበት ታማኝ ሠራዊት ያለው ኢሕአዴግ ቀድሞ ይለወጣል ብሎ መጠበቅ የፖለቲካ የዋህነት ይመስለኛል፡፡ ኢሕአዴግን ጭምር ለመታደግ፣ የምር የቤት ሥራዎቻችንን መሥራት ይኖርብናል፡፡ ሁሌ የራሳችንን የቤት ሥራ ሳንሠራ፤ የኢሕአደግንም ሆነ የፈረንጆቹን በሮች ማንኳኳቱ የትም እየወሰደን አይደለም፡፡ ፖለቲካ ለሚገባው ሰው እስካሁን ያለው የዓመታት ተሞክሮዎቻችን የሚያሰየው

ይህንኑን ሐቅ ነው፡፡ ይበልጥ የሚያሳስበው ድግሞ፤ ተቃዋሚዎች በተደጋጋሚ ከገበቡት የፖለቲካ ቅርቃር ለመውጣት የተደረጉ ጥረቶችም ያለመሰካታቸው ነው፡፡ አንጋፋ በሚባሉ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች መኢሶንና ኢህአፓ የተከፈተው የመከፋፈል ፖለቲካ ዛሬም በስፋት ቀጥለዋል፡፡ አንዱ ቀዳዳ ሲዘጋ ሌላው ቀዳዳ እየተከፈተ መፍትሄው ለወዳጅም፣ ለጠላትም ያስቸገረ ይመስለኛል፡፡ የሦስትዮሽ መሥመር ክፍፍሉን የበለጠ የሚያበላሹ ተቃዋሚን እንዲቃወሙ ኢሕአዴግ ያደራጃቸውና የሚቀልባቸው ብቻ ሳይሆኑ፤ በየድርጅቶቹ እግር ጥሎዋቸው ከግል ዝና ያለፈ የፖለቲካ ዓላማ የሌላቸው ግለሰቦችም አሉ፡፡ ተባብሮ መታገል እልህ አስጨራሽ ሥራ የሆነው በነዚሁ ምክንያቶች መሆኑ ብዙም አያከራክርም፡፡ በተለይ የሚጋጩ ሕልሞችን ይዞ የተባበረ ትግል ውስጥ መግባት ቀላል ጨዋታ አልሆነም፡፡ ተነጋግረን ጨርሰናል ካልን በኋላ ‹‹እስቲ ከሰዎቼ ጋር ተማክሬ›› የሚሉ የፖለቲካ መሪዎች ብዙ ጊዜ አጋጥሞኛል፡፡ እነዚህ ዓይነት ሰዎች ብዙውን ጊዜ አዎንታዊ መልስ ይዘው አይመለሱም፡፡ ጥርጣሬዬ እነዚህ አማካሪ የሚባሉ ሰዎች ሲያንስ ፖለቲካ ጫርሶ ያልገባቸው መንገደኞች፤ ሲበዛ ደግሞ ኢሕአዴግ ያስቀመጣቸው ሥውር እጆች ይመስሉኛል፡፡ የተሻለ የፖለቲካ እውቀትና ግንዛቤ እንደሌላቸው ግን እርግጠኛ መሆን ይቻላል፡፡ የተሻለ የፖለቲካ እውቀትና ግንዛቤ ቢኖራቸው እንደዛ የሚሉኝ ሰዎች የሚመሩዋቸው ድርጅቶች የተሻሉ ሥራዎችን ሲሠሩ ይታይ ነበር፡፡

የተቃዋሚው ኃይል ከገባበት የፖለቲካ ቅርቃር (dead-end) ለመውጣት ራሱን እንደገና ማደራጀት አለበት፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ አዲስ የመሰባሰብ እስትራቴጂ መቀየስ አለበት፡፡ ነጻ የሆኑ የተቃዋሚ ድርጅቶች (ኢሕአዴግ በቀጥታም ሆነ በሥውር እጆቹ የማይቆጣጠራቸው) በቁርጠኝነት የሀገሪቱን ችግሮች የሚፈቱበትን ዲሞክራሲያዊ ጨዋታ (democratic game) ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡ የእንዲህ ዓይነቱ ጨዋታ ውጤት የሚያመጣው በአንድ ቡድን ወይም ሁለት ቡድኖች የተረጋጋች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መፍጠር ይቻላል የሚለው ሕልም ሲቀር መሆኑን በውል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ቡደን ሥር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት ይቅርና፣ የተሻለ እድገት እንኳ ማምጣት እንዳልተቻለ የቅርብ ታሪካችን በቂ ምስክር ነው፡፡ አፄ ኃይለሥላሴ ሥልጠናቸውን ሳያጋሩ ዘመናዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር ከማንም በላይ ሞክረዋል፡፡ በተወሰኑ አካባቢዎች ‹‹የአባባ ጃንሆይ›› ትውስታ ቢንፀባረቅም ኋላቀር የዘውድ አገዛዛቸው ለ20ኛው ክፍለ ዘመን የሚሆን ሥርዓት አልነበረም፡፡ ኪሣራው ደግሞ ለሀገር ብቻ ሳይሆን ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸውም የከፋ ነበር፡፡ የእሳቸው ዓይነት አገዛዞች በዓለም ላይ የቀሩት በዓረቡ ዓለም ብቻ ሲሆኑ፤ እነሱም ቢሆኑ ያሉት በሕዝባቸው ድጋፍ ሳይሆን፤ ምዕራባዊው ዓለም በተለይ አሜሪካ ይህን በዘይት የበለፀገ አካባቢን ለመቆጣጠር ሰፊ ወታደራዊ ድጋፍ ስለምታደርግላቸው ነው፡፡ ደርግም በሶቪየቶች እርዳታ ሞክሮዋል፡፡ ሙከራው በደርግ መንግሥት ሞት ነበር፤ የታጠናቀቀው፡፡ ኢሕአዴግ ለ24 ዓመታት የአንድ ቡድንን ሕልም አሳካለሁ ብሎ ራሱም ታምሶ ሕዝብን ቢያምስም፣ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ስትፈጠር እያየን አይደለም፡፡ ከሠሩት ሥራ የፕሮፓጋንዳ ጫጫታቸው እንደሚበልጥ የኢሕአዴግ መሪዎችም ያውቁታል፡፡ ከላይ ደጋግሜ እንዳነሳሁት፣ አሁን በገፉበት መንገድ ከቀጠሉ ዕጣ ፈንታቸው ከንጉሡና ደርግ ለመሻሉ ምንም ዋስትና የለም፡፡ ወደ መቶ ሚሊዮን

እየሆነ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕልምና ፍላጐቱ ከኢሕአዴግ መሪዎችና ካድሬዎቹ ሕልምና ፍላጐት በጣም ይሰፋል፡፡

በመደምደሚያዬም የሚከተለውን መልእክት ማስተላልፍ እፈልጋለሁ፤ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታ የተቃዋሚው ኃይል እንደገና ራሱን ቢያደራጅ፣ የኢትዮጵያ የነፃነት ቀን ሩቅ አይመስለኝም፡፡ የማይታረቁ ሕልሞቹን ተሸክሞ በምኞች ፈረስ መጋለቡን ከቀጠለ ግን፤ ሕልሞቹ ሕልም ከመሆን አያልፉም፡፡ የቡዳ ፖለቲካችንን ተሸክመን ላለፉት አርባ ዓመታት ኳትነናል፣ ለሚቀጥሉት አርባ ዓመታትም በያዝነው መንገድ ብንኳትንም የትም አንደርስም፡፡ ስለሆነም፣ የተቃዋሚ ኃይል ነን የምንለው፤ እስካሁን ላለፉት አርባ ዓመታት የሠራናቸውን ስህተቶች ባረመ መልኩ በአዲስ መንፈስ፣ በጋራ ሕልም ዙሪያ እንደገና በሀገር ውስጥም፤ ውጭም መደረጀት የግድ ይመስለኛል፡፡ ውጤት አልባ ለሆነው የተበታተነ ትግል የሚባክነውን የሀገር ሀብት ወንዝ ሊያሻግር ለሚችል የጋራ ትግል ማዋልም የግድ ነው፡፡ የሁላችንም የፖለቲካ መንግሥት ሰማያት ሁላችንንም በእኩልነት የምታስተናግድ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር ለነገ የምንለው መሆን የለበትም፡፡ የጋራ የታሪክ ፈተናችን ለማለፍና የጋራ ሕልማችን እውን ለማድረግ የሰከነ ትግል፣ አቅም ላይ የተመሠረተ ትግል፣ የተደረጀና የተባበረ ትግል ውስጥ በሐቅ፤ በፍጥነትና በቁርጠኝነት እንድንገባ አደራ እላለሁ፡፡

---

ሀሰቦቹ የተወሰዱት፤ **የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅል ጉዞና የሕይወቴ ትዝታዎች፤ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ እስከ ኢህአዴግ** (2006) ከሚለው መጽሐፌና **የኢትዮጵያ የታሪክ ፈተናዎች እና የሚጋጩ ሕልሞች፤ የኢህአዴግ ቆርጦ-ቀጥል ፖለቲካ** (2008) ከሚለው መጽሐፌ ነው፡፡